**የዲሲ መንግስት (GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA)**
**የጤና እንክብካቤ ፋይናንስ መምሪያ (Department of Health Care Finance)**

## የህብረት እና የስደተኛ ልጆች ፕሮግራም እድሳት እንደገና መጀመር በተዳጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች (FAQ)

**ዓላማ፡** የዚህ ሰነድ ዓላማ የህብረት (Alliance) እና የስደተኛ ልጆች መርሃ-ግብር (አይ ሲ ፒ- ICP) ዕድሳት መጀመሩን ለማሳወቅ እና ከዳግም ማስጀመር ጋር በተገናኘ በተደጋጋሚ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ነው።

1. **የአሊያንስ (Alliance ) እና የአይሲፒ (ICP) ዕድሳት እንደገና የሚጀምረው መቼ ነው?**

   ሽፋናቸው (coverage) እስከ ኦገስት 31፣ 2022 መታደስ ላላበት ቤተሰቦች፤ ዕድሳቶች በጁላይ 1 ቀን 2022 እንደገና የሚጀመሩ ሲሆን፤ ከዚያ በኋላ ተጠቅሚው ሽፋኑን እንዲያድስ በታቀደበት ቀን ላይ በመመርኮዝ እንደጊዜው የሚከናወን ይሆናል።

2. **የአሊያንስ (Alliance ) እና የአይሲፒ (ICP) ዕድሳት እንደገና መጀመር በሜዲኬይድ ሽፋን (Medicaid coverage) ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል?**

   የአሊያንስ (Alliance) እና አይሲፒ (ICP) በክልል ገንዘብ የሚደገፉ መርሃ-ግብሮች ናቸው፤ እናም በፌዴራል ገንዘብ የሚደገፈው ሜዲኬይድ (Medicaid) ላይ ተጽእኖ አይኖረውም። የፌደራል የህዝብ ጤና ድንገተኛ አደጋ አሁንም በስራ ላይ ነው እና ቀጣይነት ያለው የሽፋን ጥበቃዎች (coverage protections) እንደቀጠሉ ናቸው። የአሊያንስ (Alliance) ወይም አይሲፒ (ICP) ተጠቃሚ በእድሳት ጊዜ ለሜዲኬይድ (Medicaid) ብቁ እንደሆነ ከተረጋገጠ ግለሰቡ ወደ ሜዲኬይድ (Medicaid) ዝፋን ይሸጋገራል።

3. **የህብረት (Alliance ) እና የአይሲፒ (ICP) ተጠቃሚዎች ዕድሳት ካጠናቀቁበት የመጨረሻ ጊዜ ወዲህ ምን ተለውጧል?**

   የአሊያንስ (Alliance) እና አይሲፒ (ICP) ተጠቃሚዎች ከአሁን በኋላ ለማደስ እንደመስፈርት ፊትለፊት ቃለ-መጠይቅ ማጠናቀቅ አይጠበቅባቸውም። ከኦክቶበር 2022 ጀምሮ፣ የአሊያንስ (Alliance) ማረጋገጫ ጊዜዎች ከ6 ወራት ይልቅ 12 ወራት ይሆናሉ። በኦገስት እና ሴፕቴምበር ማሳደስ ያለባቸው ቤተሰቦች በመጀመሪያ ለ6 ወራት ከዚያም ለ12 ወራት፤ በሚቀጥለው ማሳደስ ጊዜ ማለት ነው፤ ይረጋገጣሉ።

   በተጨማሪም፣ የገቢ ገደቡ ከዚህ በታች ከሚታዩ የኤምኤጂአይ ሜዲኬይድ (MAGI Medicaid) ደረጃዎች እና የገቢ ደረጃዎች ጋር በማጣጣም ተሻሽሏል። የአሊያንስ (Alliance) መርሃ-ግብር $4000 ለ 1 ቤተሰብ እና $6000 ለ2 ቤተሰብ የሃብት ምዘና (resource test) የለውም። የአሊያንስ (Alliance) ተጠቃሚዎች ከአሁን በኋላ በሚያሳድሱ ጊዜ የቼኪንግ ወይም የቁጠባ ሂሳብ ዝርዝር ማቅረብ አይጠበቅባችውም።

   አሊያንስ (Alliance)

| **የቤተሰብ መጠን (Household Size)** | **የዲሲ የጤና እንክብካቤ አሊያንስ መርሃ-ግብር (DC Health Care Alliance Program)** |
|---|---|
| | **210% +5% ገቢን ያልተመከከተ (Income disregard)** |
| 1 ሰው ቤተሰብ፤ በየወሩ | $2,434.88 |
| 2 ሰው ቤተሰብ፤ በየወሩ | $3,280.54 |
| 3 ሰው ቤተሰብ፤ በየወሩ | $4,126.21 |
| 4 ሰው ቤተሰብ፤ በየወሩ | $4,971.88 |
| 5 ሰው ቤተሰብ፤ በየወሩ | $5,817.54 |

የስደተኛ ልጆች መርሃ-ግብር (Immigrant Children's Program (ICP))

| **የቤተሰብ መጠን (Household Size)** | **ልጆች (0-18), 319%** | **ልጆች (19-20)** |
|---|---|---|
| | **319% + 5% ያልተመለከተ (disregard)** | **216% + 5% ያልተመለከተ (disregard)** |
| 1 ሰው ቤተሰብ፤ በየወሩ | $3,669 | $2,502 |
| 2 ሰው ቤተሰብ፤ በየወሩ | $4,943 | $3,372 |
| 3 ሰው ቤተሰብ፤ በየወሩ | $6,218 | $4,241 |
| 4 ሰው ቤተሰብ፤ በየወሩ | $7,492 | $5,110 |
| 5 ሰው ቤተሰብ፤ በየወሩ | $8,766 | $5,979 |

## 4. How can የአሊያንስ (Alliance) እና አይሲፒ (ICP) ተጠቃሚዎች ሽፋናቸውን እንዴት ማደስ ይችላሉ?

**ኦንላይን (Online)**: በኖቬምበር 2021 ዲስትሪክቱ (District) አሊያንስ (Alliance) እና አይሲፒን (ICP) ወደ ዲስትሪክቱ ቀጥተኛ ብቁነት ስርዓት (District Direct eligibility system) ጨምሮታል፤ ይህም ዕድሳታቸውን እንዲያጠናቅቁ፤ ለውጦችን እንዲያሳውቁ፤ ማረጋገጫዎችን እንዲያቀርቡ፤ እና ማስታወቂያዎችን በኦንላይን (online) ወይም በተንቀሳቃሽ ስልክ መተግበሪያ (app) በኩል እንዲመለከቱ ያስችላቸዋል።.

ተጠቃሚዎች visit https://districtdirect.dc.gov/ ድረ-ገጽን መጎብኘት ወይም በአፕል አፕ ስቶር (Apple App Store) ወይም ጉግል ፕሌይ (Google Play) በኩል የተንቀሳቃሽ ስልክ መተግበሪያን ማውረድ (download the mobile app) ይችላሉ።

መጀመሪያ የራስዎን መለያ (account) በመፍጠር ዲስትሪክት ዲረክትን (District Direct) ማግኘት ይችላሉ። የራስዎ መለያ (account) ከሌለዎት፤ በ districtdirect.dc.gov በኩል የራስዎን መለያ (account) መፍጠር ይችላሉ፤ ወይም ደግሞ በ ዲስትሪክት ዳይረክት ሞባይል አፕሊኬሽን (District Direct Mobile Application) በኩል (ይህም በ ጉግል ፕሌይ (Google Play) ወይም አፕል አፕ ስቶርስ (Apple App Stores) ላይ ይገኛል)።

ዋናው ገጽ ላይ፤ "ሎግ ኢን" ("Login") የሚለውን ይጫኑ፤ ከዚያም "አካውንት ይፍጠሩ" ("Create Account") የሚለውን ይጫኑ። በሚቀጥለው ገጽ፤ የራስዎን መለያ ("account") ለመፍጠር የሚያስፈልገውን መረጃ ያስገቡ (ለምሳሌ፤ መጠቀሚያ ስም (username) ማለፊያ ቃል (password))።

ይህ ካለቀ በኋላ፤ መለያ ቃል ይፍጠሩ ("Create Account") የሚለውን ይጫኑ። መለያዎን (account) ከፈጠሩ በኋላ "መለያዎን ያገናኙ" ("Connect Your Account") የሚለውን በመጫን በ ዋናው ገጽ ላይ አስፈላጊውን መረጃ በማስገባት መለያዎን (account) ያገናኙ። መለያዎ (account) ከተገናኘ በኋላ፤ መረጃዎን ለማየት ወደ መነሻ ገጹ (homepage) ይመለሱ።

የራስዎ መለያ (account) ካለዎት፤ በ districtdirect.dc.gov በኩል ወይም ደግሞ በ ዲስትሪክት ዳይረክት ሞባይል አፕሊኬሽን (District Direct Mobile Application) በኩል (ይህም በ ጉግል ፕሌይ (Google Play) ወይም አፕል አፕ ስቶርስ (Apple App Stores) ላይ ይገኛል) ማግኘት ይችላሉ። መለያዎን (account) ለመጠቀም የመጠቀሚያ ስምዎን (User ID) እና ማለፊያ ቃል (Password) ማስገባት አለብዎት። በኦንላይን (online) ለጥቅማጥቅሞች (benefits) አመልክተው ከሆነ፤ በሚያመለክቱበት ወቅት የመጠቀሚያ ስም (User ID) እና ማለፊያ ቃል (Password) ፈጥረዋል።

መጠቀሚያ ስምዎን (Username) ወይም ማለፊያ ቃልዎን (Password) ረስተው ከሆነ፤ "ማለፊያ ቃል እረሳሁ" ("Forgot Password") ወይም "መጠቀሚያ ስም እረሳሁ" ("Forgot Username") የሚለውን ሊንክ በመጫን

ወይም የዲስትሪክት ዳይረክት (District Direct) የደንበኛ ስልክ መስመር በ 1-202-727-5355 በመደወል እንደገና ማስተካከል ይችላሉ።

**በፖስታ:** ተጠቃሚዎቹ እድሳትን በፖስታ ወደሚከተለው አድራሻ መላክ ይችላሉ፤
Department of Human Services | Economic Security Administration
Case Record Management Unit
P.O. Box 91560
Washington, DC 20090

**በአካል:** ተጠቃሚዎች የእድሳት ቅጻቸውን ለሰው አገልግሎት መምሪያ (Department of Human Services) ማእከል ማቅረብ ይችላሉ።

**በ ፋክስ:** ማመልከቻውን በ (202) 671-4400 ፋክስ ያድርጉ።

### 5. በእድሳት ወቅት ምን ማረጋገጫዎች ያስፈልጋሉ?

የአሊያንስ (Alliance) ተጠቃሚዎች የዲስትሪክት (District) ነዋሪነት እና የገቢ ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው። ለአይሲፒ (ICP)፤ የወላጅ ገቢ ከእድሳት ቅጹ ጋር መቅረብ አለበት። የነዋሪነት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው እድሜያቸው 20 ዓመት ለሆኑ የአይሲፒ (ICP) ተጠቃሚዎች ብቻ ነው። .

| **የማረጋገጫ ዓይነት** | **ተቀባይነት ያላቸው ማረጋገጫዎች** |
|---|---|
| **ገቢ** | • የቅርብ ጊዜ ክፍያዎች (paystubs) (ካለፉት 30 ቀናት)<br>• የግል ስራ (Self-employment): የቅርብ ጊዜ የታክስ ሰነድ (tax return form)<br>• የጡረታ ገቢን የሚያሳይ ማረጋገጫ<br>• የአካል ጉዳት ገቢ (Disability income)<br>• የሰራተኞች ማካካሻ (Workers Compensation)<br>• የጡረታ ወይም አበል ማረጋገጫ (Pension or annuity statement)<br>የስራ-አጥነት ጥቅማጥቅሞች ማስረጃ (Unemployment benefit statements) |
| **ነዋሪነት (Residency) (ዓንድ ዓይነት ማረጋገጫ ብቻ ያስፈልጋል)** | • የዲሲ (DC) መንጃ ፈቃድ፤ መታወቂያ ካርድ፤ ወይም ዲሲ ዋን ካርድ (DC One Card)<br>• ወቅታዊ የሆነ የኪራይ ውል፤ ስምምነት ወይም የኪራይ ደረሰኝ<br>• የአገልግሎት (Utility) ወይም የስልክ ሂሳብ<br>• ባለፉት 30 ቀናት ውስጥ የግለሰቢን ስም እና የዲሲ (District of Columbia) አድራሻ የያዘ የክፍያ ወረቀት ወይም የገቢ ማረጋገጫ<br>• በዲሲ (District of Columbia) ውስጥ ለሚገኝ ንብረት ባለፉት 60 ቀናት ውስጥ የወጣ የንብረት ታክስ ሂሳብ<br>• የተሞላ የነዋሪነት ቅጽ |

**ስለ አሊያንስ (Alliance) እና አይሲፒ (ICP) እንደገና ማስጀመር በሚመለከት ላሉ ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ለሚነሱ ጥያቄዎች (FAQ) DHCFAllianceRecert@dc.gov ን ያግኙ።**

**ምንም ዓይነት ጥያቄ ካለዎት ከሰኞ እስከ ዓርብ፤ ከ7:30 ኤኤም እስከ 4:45 ፒኤም በ 202-727-5355 መደወል ይችላሉ።**